# ወርደ ሰፊው የስንብት ቀለማት በጊዜና በማህበራዊ ህፀፅ አንጻር ቅንጫቢ ማሳያ

አንተነህ ከበደ

ለዘመናችን ብቻ ሳይሆን ለአጠቃላይ የኢትዮጵያ ስነ-ፅሑፍ፣ ክስተትም ታላቅ ስጦታም ነው ደራሲ አዳም ረታ:: እንደ አንባቢና የስነ-ፅሑፍ ጋዜጠኛ ጭምር ለአዳም ያለኝን ጥልቅ ስሜት የምገልፅበት አረፍተ ነገር ለሱም እንደምለው "ዘመንህን ስለተጋራሁህ እጅግ በጣም እድለኛ ነኝ" የሚል ነው፡፡ በታሪክ ወይ በስማ በለው ልክ "በአንድ ወቅት አዳም ረታ የሚባል ደራሲ ነበረ" አይነት ትርክት ቢሆን ዕውቂያዬ እዴት ይቆጨኝ ነበር እንደማለት፡፡

ለማንኛውም ይህ መንደርደሪያ ወርደ ሰፊውን የአዳም ረታና የኢትዮጵያ ስነ-ፅሑፍ ረጅም ልብ ወለድ የስንብት ቀለማት በጥቂቱ ለመቃኘት የተደረገ ሙከራ ነው፡፡ ሙከራው ትኩረቱ የአዳምን በልብ ወለድ ውስጥ የጊዜ አጠቃቀምንና ማህበራዊ ህፀፅ ማሳያ ጥቂት ነጥቦችን ለማጋራት ነው፡፡

መፅሐፉ 932 ገጾችን የያዘ ነው፡፡ የስንብት ቀለማት በአፍታ ውስጥ የተዘረጉ እልፍ አዝማናትን ለትርክት ጊዜው (time) የመረጠ ሲሆን ፤አፍታው ከመፅሐፉ ርዕስ ጋር ተዛምዶ ባለው ስንብት ወይም የአስከሬን ሽኝት ላይ የምትፈጠርን አንዲትን አፍታ በክብ (እንጀራዊ ወይም እንጀሪያዊ) የትረካ ስልቱ በየሸኚው ህይወት ዙሪያ ከተሸኚው ጋር ያለውን ተዛምዶና፤ አውዱ ቀብር እንደመሆኑ አንዱ ቀባሪ ከሌላው ቀባሪ ጋር ባለውም የህይወት ትስስር ውስጥ የተሸመነ ተረክ ነው፡፡ ይህ ትስስር ሁለተኛውንና እልፍ ዘመናትን በውስጡ ያዘለውን ሁለተኛውን ጊዜ (ታይም) ይወልዳል፡፡ በዚህ በሁለተኛው ጊዜ ውስጥ በተረት በምናውቀው ስንዝሮ አማካኝነት የተረኩን ዘመን ሁለት ሶስት ሺህ ዓመታት ወደኋላ በመለጠጥና ብሩህ ተስፋን ደግሞ ትናንትን ከዛሬ አዋህዶ ከስንዝሮና ከምትክ ሪችዋል አይነት ሩካቤ በሚፈጥረው አዲስ ፍጥረት የነገ ገፀ ተስፋ አማካኝነት ቀጣይነትን ተልሞ ተረኩን ማለቂያ ወደሌለው ነገ ሲዘረጋው ስናይ፤ ጊዜን እዳሻው እንደሚዘረጋና እንደሚያጥፈው ፈጣሪ ያክል የረቀቀ የጊዜ ፈጣሪነቱን ለመመስከር እንገደዳለን፡፡ አዳም ከዚህ በፊት አንባቢዎቹን ሁሉ በእጅጉ የሚያስደንቅበት የቦታ ፈጠራው ንፋስ መውጫ በግራጫ ቃጭሎች፣ ሽሮ ሜዳ በመረቅ፣ ወንበራ በይወስዳል መንገድ ያመጣል መንገድና በዚህ የስንብት ቀለማት ደግሞ ንፋስ ስልክ ሲሆን፤ በዚህኛው ልብ ወለድ ስራው የቦታ ፈጠራን ብቻ ሳይሆን የጊዜን ፈጠራም ያሳየበት ክስተት ነው የስንብት ቀለማት፡፡ ማቱሳላን በዕድሜ የሚያስከነዳው ስንዝሮ በሺህ ዘመናት ውስጥ ሲመላለስ እንደ አንባቢ ጊዜውን አብረንው እንሻገራለን እንጂ ፍፁም አይጎረብጠንም፡፡ ለዚህ ነው የጊዜ ፈጠራው ክስተት ነው የምንለው፡፡ ብዙ ሺህ ዘመናት ሲኖርና ለብዙ አመታት ሲተኛ ኮምፐሌን አናደርግም፡፡ እረ የማይመስል ነገር ብለን የታሪኩን ፍሰት በተጠየቅ አንሞግትም ይልቅ እንደ መልካም አጃቢ አብረን ረጅሙን የጊዜ ድልደይ እንራመዳለን እንጂ::

ደራሲያን ጊዜን ለትርክታቸው እነደሚስማማ አድርገው ይጠቀሙበታል፡፡ የምናባዊ ተረኮች ለምሳሌ እንደ ሀሪ ፖተር ያሉት ጊዜን በተመለከተ ያላቸው መረጃ ድንግዝግዝ ሲሆን ያም የተረኩ አንድ አካል ነው፡፡ አዳም ከስንብት ቀለማት በፊት ባሉት የድርሰት ስራዎቹ ጊዜን ለትርክቱ እንደሚስማማ የሚጠቀምበት ሲሆን በዋናነት ከ1960 ዎቹ ህይወትና ኑሮ ጋር የተቆራኙ ጊዜዎችን ደጋግሞ አስነብቦናል፡፡ ዘመነ ኢህአፓ የምንለውን፡፡ መዝገቡም ለዘማቾች ወረቀት በትኗል፣ እነ አላዛርም በደርግ በእስር ተሰቃይተዋል፣ ሎሚ ሽታም፣ ማህሌትም ወዘተ በእጅጉ ከዚህ ዘመን ጋር የተሳሰሩ የአዳም የፈጠራ ውጤቶች ናቸው፡፡ በስንብት ቀለማት ውስጥ አዳም ጊዜን ከመጠቀም የተለምዶ የድርሰት ስልት ወጥቶ ጊዜን የመፍጠር ስራ ሲሰራ እንመለከተዋለን፡፡

ለዚህ ለጊዜ ፈጠራ ዋነኛ ማጠንጠኛ የሆነውና ሺህ ዓመት ይንገሱ የሚለውን አይመስል ፀሎታችንን በተግባር የኖረው የስንዝሮ ትዕምርታዊነቱ ውስጥ የሃገራችን ውክልና አለበት፡፡ አንዱ የስንዘሮ ጠባይ ረጅም ጊዜ መተኛት ነው፡፡ 40 ዓመት አንዳንዴም ወደ100 ዓመታትም እየተኛ ይነሳል፡፡ ሌላው ደግሞ መስታወት መጥላቱ ነው፡፡ ራስህን በመስታወትም ይሁን በውሃ ካየህ ትሞታለህ ተብሏልና፡፡ ይህ ባህሪው ነው እንግዲህ ኢትዮጵያን ያሰመስለዋል ያስባለኝ፡፡

ለዘመናት እየተኛ መነሳቱ ያው አክሱምን ስርታ ተኝታ ደግሞ ትነቃና ላሊበላን፤ ሌላ ረጅም እንቅልፍ፤ ፋሲልን ...እንደገና እንቅልፍ...፡፡ የኢትዮጵያ ታሪክ አብዛኛው እንቅልፍ ጥቂቱ ስራ ነው፡፡ ልክ እንደ አዳም ረታ ስንዝሮ፡፡ ሁለተኛው ራስን የማየት ርግማን፤ ከራስ የመሸሽ ርግማን ነው፡፡ ራሳችንን ስናይ ውበት ማስጠላታችንን፤ ድክመት ጥንካሬአችንን የማየት አቅም ይሰጠናል፡፡ መስታወት እርማችን ከሆነ ግን ምን ሊሆን እንደሚችል አስቡት፡፡ እነዚህ የዘመን ህፀፃችንን ለማስተንተንና የተዋጣለት ማህበራዊ ሂስ ለመሰንዘር የጊዜ ፈጠራ ግድ በማለቱ ነው አዳም ከጊዜ መጠቀም ወደ ጊዜ ፈጠራ የተሻገረው፡፡

ስለጊዜ አጠቃቀሙ ይህንን ካልኩኝ ሁለተኛውንና የማህበራዊ ህፀፅ ማሳያ ሃሳቡን ጥቂት ልምዘዝ፡፡ መፅሐፉ በመጀመሪያ ገፁ ላይ ከባድ ማህበራዊ ትችት ሰንዝሮ ነው የሚነሳው፡፡ “እስኪ አሳዩኝ ለአገራችሁና ለመዲናችሁ የነደፋችሁትንና የተዋጣላችሁን ሰናይ እቅድ? እሱንም ያስቀመጣችሁበት ስፋራ? ትናንት ካንደባለላችሁ ዠላጣ ወደ አማረው ኮረብታ መንገድ ቀይራችኋል? ይህቺ ቀበሌያችሁ ንፁህ ውሃ ቢያጥራት ወደ መልካም አዲስ ነገር ተጠምቃችሁ ማለፍ ስላላቻላችሁ ነው፡፡ የጎዳናዎቻቸሁ የትራፊክ መብራት ነጋ ጠባ ባይበራ፣ የምትሄዱት ወደየት እንደሆነ የማታውቁ ራዕየ-ቢስ ስለሆናችሁ ነው፡፡ ትምህርት ቤቶቻቸሁ ቢቆረቁዙና ቢፈርሱ፣ ዘር ማንዘራችሁ መደንቆር ቢወድ ነው፡፡ ከተማችሁ ብትሸት እንደዛ መሆኗን ስለሻታችሁ ነው፡፡ በየቤታችሁ መብራት ባይኖራችሁ ነፍሳችሁ ስለጨለመ ነው ....ታዲያ ስለምን ቀደም ቀደም ብላችሁ ፀሐይ ገና ከማዘቅዘቋ ትተኛላችሁ? ረእይ ባይኖራችሁና በየአልጋችሁ ላይ ተንጋላችሁ ኑሮን በፅላሎት ለመገላገል አቅዳችሁ ካልሆነ?”

ይህ ከባድ ዱላ ነው፡፡ በርግጥ የተበላሸ መንገዳችንን ከማንኳጠጥ አልፈን እያነሳ የሚያፈርጠንን ዠላጣ አቃንተናል...ይህ ትርክት የህንዳዊውን ታሪክ ለማስታወስ ያስገድደናል፡፡ ህንዳዊው ከመንደራቸው ወደ አቅራቢያ ሆስፒታል የሚወስደው መንገድ እጅግ እሩቅና ምቹ አለመሆኑን ከሚያማርሩ የመንደሩ ነዋሪዎች አንዱ ነበሩ፤ ታዲያ አንድ ቀን ይህንን ምሬት ወደጎን ጥለው አንዲት መጥረቢያ አንስተው ተራራውን በመቦርቦር መንገድ ለመስራት ተነሱ፡፡ በግለሰብ አቅማቸው መቦርቦር የጀመሩት የተራራ ውስጥ ለውስጥ መንገድ ከ22 ዓመታት ብሩቱ ልፋትና ያልተበገረ ፅናት በኋላ 70 ኪሎሜትሩን አስቸጋሪ መንገድ ወደ 1 ኪሎሜትር ጥርጊያ ቀይሮ ሆስፒታሉን ወደመንደራቸው አስጠግቶታል፡፡ አዳም ይህንን ነው የሚጠይቀን፡፡ በዚህ ጥያቄ ውስጥ መንገድ የሚለው ቃል ከግለሰብ ተጠያቂነት ለማምለጥ የማርያም መንገድ ይመስለን ይሆናል፤ ግን አለመሆኑን የዚህ ህንዳዊ ታርክ ያሳጣናል፡፡ ብሎም እንደ ግለሰብ ከየራስ ጉዟችን እያዳለጠ ከሚያፈርጠን እንቅፋት ስንቱን አስወገድን? የሚል እንደምታም አለው፡፡ ውሃም ቢያጥረን የትናንትና መጥፎ ታሪካችንን በይቅርታ ጠበል ተረጭተን ወደመልካም አዲስ ነገር ለማለፍ የማመፃችን ማሳያ ነው፡፡ ይህ የሚያም የታሪካችን፣ የፖለቲካችንና የማህበራዊ ስንክሳራችን ያፈጠጠ ሃቅ ነው፡፡ የምንድነው ሳይሆን ሰርክ የምናስታምመው ቁስላችን፡፡

ታላቁ መፅሐፍ “ራዕይ ሌለው ህዘብ ይጠፋል” ይላል፡፡ አዳም ረታ የጎዳናችን መብራት ቢስ መሆኑ የጉዞአችንን አቅጣጫ ያለማወቃችን ምልክት ነው ይለናል፡፡ የልባችን ብርሃንም መደንገዝ፡፡ ዕውቀት የነገር ሁሉ መሰረት ነው፡፡ እኛ ግን እንደ ማህበረሰብ ዕውቀትን እየሸሸን፣ ጥበብና ማስተዋልን እየገፋን ወደማያንፅ ድንግዝግዝ እየተጓዝን ለመሆናችን ሚዲያችንን የሞሉትን ርባና ቢስ ፕሮግራሞች በማየት ብቻ የዝንጋኤያችንን ጥልቀት

መገንዘብ እንችላለል፡፡ ለሱም ልብ ካለን ማለት ነው፡፡ ትምህርትና የዕውቀት መስካችን መቆርቆዙ ብሎም መፍረሱን ያየው አዳም አላባበለንም፤ ከቶም አላስታመመንም ይልቅም ዘር ማንዘራችሁ መደንቆር ቢወድ ነው ብሎ ቁርጣችንን ይነግረናል፡፡ ድንቁርናን መውደዳችንን ብቻ አይደለም የተቸው ለዘር ለማስተላለፍ በትጋት እየሰራን ያለን የድንቁርና ገበሬነታችንንም ጭምር እንጂ፡፡ እንዴት ያማል፡፡ ድንቁርና እየዘሩ መሃይምንት ማጨድ፡፡ የዕውቀት ጠልነት ዘርን ለትውልድ የማውረስ አፍቃሬ ጨለማነት፡፡ እንዴት ያስፈራል፡፡ በቤታችሁ መብራት ባይኖር ነፍሳችሁ ስለጨለመ ነው ይለናል፡፡ ድሮስ የዕውቀት አውዱን ያቆረቆዘ የጥበብ ብርሃን ከየት ሊጨልፍ፡፡ ለዚህም ይመስላል አዳም በስጋ እንደተመላለሰባቸው የአውሮፓና የአሜሪካ ሃገራት የከተማችንና የቤታችንን ብርሃን ለኩሰን የዕውቀት አድማሳችንን አስፍተን ለስራ ዘወትር 24 ሰዓታት ከመታተር ይልቅ በጊዜ ካሊም ተጠቅለን በዕውን ማግኘት ያቃተንን ስኬት በቅዠት ለመውለድ የምንቃትት የአብርሆት ጠር መሆናችንን የሚያዳን፡፡

ይህን ለማየትም ለመቀበልም አቅም ይጠይቃል፡፡ በተለይ እንደኛ በታሪክና በሃይማኖት ካባ ተኮፍሶ (ከኛ በላይ ባለታሪክ ከኛ በላይ ሃይማኖተኛ የለም) በማለት ለሚመጻደቅ ማህበረሰብ የአደባባያችንን፣ የቤታችንንና የልባችንን ጨለማ ሳይቀር በሰርሰሪ አይኖቹ ተመልክቶ ለአንባቢው ፍንትው ፍትት አድርገው በሚያመላክቱ ጥልቅ ትዝብቶች ገባድ የሃሳብ ጦሮች ሰንዝሮ ነው አዳም ረጅሙን ልብ ወለዱን የሚጀምረው፡፡ ይህ ገና በገፅ 1 ላይ ያለ ትችት ነው፡፡ ለማንኛውምየስንብት ቀለማትን ለንባብ እየጋበዝኩ እዚህ ጋር እልባት ማድረግ ሳይሻለኝ አይቀርም፡፡ መልካም ንባብ፡፡